DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

# ለቤተሰቦች፥

# የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅ ምንድን ነው?

በዲሲ የሕዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ የመግቢያ ሂደት አካል፣ ሁሉም ወላጆች እና አሳዳጊዎች የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅን በሚቀጥለው ገጽ ላይ መሙላት አለባቸው።

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ማጣሪያ ( አጭር ፈተና) ለመውሰድ ልጅዎ ብቁ እንደሆነ ለማወቅ ትምህርት ቤቶች የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅን ይጠቀማሉ። ማጣሪያው ልጅዎ የትምህርት ቤቱ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ብቁ እንደሆነ ለማወቅ ለትምህርት ቤትዎ ያግዛል። በእንግሊዘኛ ቋንቋ ላይ ያላቸውን ብቃት እንዲያሳድጉ እና በትምህርታቸው ላይ ስኬታማ እንዲሆኑ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋ የመማሪያ ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ የፌደራል ህግ ትምህርት ቤቶችን ያስገድዳል።**ሁሉም የዲሲ ነዋሪዎች፣ ከሁሉም ዳራ የተውጣጡ፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ በሚገኙ የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ተቀባይነት አላቸው።**

የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅ ለ**ስደተኛ ጉዳይ**ዓላማ አያገለግልም።

የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅ**ይሄንን**ለመወሰን አያገለግልም፡

- የስደተኛነት ሁኔታዎን፥
- የነዋሪነት አቋምዎን፥ ወይም
- ልጅዎ የእንግሊዘኛ ተማሪ መሆኑን።

እባክዎ የቤት ውስጥ ቋንቋ መጠይቅ መሙላት ላይ ድጋፍ የሚያስፈልጎት ከሆነ ለትምህርት ቤትዎ ያሳውቁ፣ እና እባክዎ ከታች ያለው ላይ ፊርማዎን ማኖርዎን እና ቀኑን መፃፍዎን ያረጋግጡ።